የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያኛ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

21th Year No.48
ADDIS ABABA 25th May, 2015

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፬/፪ሺ፯ ዓ.ም

በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ምዕራፍ ፪ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ..........................ገጽ ፰ሺ፪፻፶፮

**CONTENTS**

Proclamation No. 894/2015

African Development Fund Loan Agreement for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme in the Horn of Africa DRSLP II Ethiopia Project Ratification Proclamation ……………………………………………page 8256

## አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፬/፪ሺ፯ ዓ.ም

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል የተደረገውን የብድር ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ምዕራፍ ፪ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ፳፰ ሚሊዮን ፬፻፹፪ሺ ዩ.ኤ (ሀያ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ዩ.ኤ) የሚያስገኘው የብድር ስምምነት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ይህንኑ የብድር ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ ፳፪ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም ባካሄደው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## PROCLAMATION No.894/2015

## A PROCLAMATION TO RATIFAY THE LOAN AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE AFRICAN DEVELOPMENT FUND

WHEREAS, a Loan Agreement, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund stipulating that the African Development Fund provide to the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia a Loan amount of 28,482,000 U.A (Twenty Eight million Four Hundred and Eight Two Thousand Units or Account) for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme in the Horn of Africa: DRSLP II Ethiopia Project was signed in Addis Ababa on the 23rd day of February 2015;

WHEREAS, the House of peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Loan Agreement at its session held on the 30th day of April 2015;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 6.45

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

**፩.አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "በተደጋጋሚ የሚከሰተውን ድርቅ በዘላቂነት ለማስወገድ ለሚያስችለው ምዕራፍ ፪ ፕሮግራም ማስፈጸሚያ የሚውል ብድር ከአፍሪካ ልማት ፈንድ ለማግኘት የተፈረመው የብድር ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፰፻፺፬/፪ሺ፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**፪. የስምምነቱ መፅደቅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በአፍሪካ ልማት ፈንድ መካከል እ.አ.አ ፌብሩዋሪ ፳፫ ቀን ፪ሺ፲፭ በአዲስ አበባ የተፈረመ የብድር ስምምነት ቁጥር 2100150032394 በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

**፫.የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር ሥልጣን**

የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በብድር ስምምነቱ የተገኘውን ፳፰ ሚሊዮን ፬፻፹፪ ሺ ዩ.ኤ. (ሀያ ስምንት ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ ሁለት ሺ ዩ.ኤ) በብድር ስምምነቱ በተመለከቱት ሁኔታዎች መሠረት በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

**፬. አዋጁ የማፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፯ ቀን ፪ሺ፯ ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

1. **Short Title**

This proclamation may be cited as the "African Development Fund Loan Agreement for financing Drought Resilience and Sustainable Livelihoods Programme in the Horn of Africa DRSLP II Ethiopia Project Ratification Proclamation No. 894/2015".

2. **Ratification of the Agreement**

The Loan Agreement Number 2100150032394 signed in Addis Ababa on the 23rd day of February 2015 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the African Development Fund is hereby ratified.

3. **Power of Ministry of Finance and Economic Development**

The Ministry of Finance and Economic Development is hereby empowered to undertake all acts necessary for the utilization of the Loan amount of 28,482,000 U.A (Twenty Eight Million Four Hundred and Eighty Two Thousand Units of Account) in accordance with the terms and conditions set forth in the Loan Agreement.

4. **Effective Date**

This proclamation shall enter into force on the day or Publication in the Federal Negarit Gazette .

**Done at Addis Ababa this 25th day of May, 2015**

**MULATU TESHOME (DR.)**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት